# <u>የእናት ሆድ ዝንጉርጉርነት ለጥፋት ወይስ ለልማት</u>?

**ከሐረገወይን፤**

በስደት በኖርኩባቸው ጊዜያት ዘወትር የሚያስቁን ነገሮች አይጠፉም ነበር። እንዲያውም ሳቅ  በጣም
ከማብዛታችን የተነሳ ደልቶት የሚኖር ሰው እንመስል ነበረና እኔ ዘወትር ራሴን እጠይቅ ነበር። ሰው
እንዴት ሰው ከመሆን አንድ ደረጃ ዝቅ ብሎ እየኖረ እንዴት ያለመጠን ይስቃል? ከዚያም ዞር ብሎ
ያነባል፤ ይበሳጫል፤ ያዝናል፤ ይተክዛል? ታዲያ ይህን ጥያቄ ለማብጠልጠል በተነሳሁ ቁጥር አእምሮዬ
ይወስድና ከአንድ እውነታ ጋር ያጋፍጠኛል። «ማሽላ እያረረ ይስቃል»።
ዛሬ ስለዚህ በቀላሉ የማይደፈር ርእስ ለመጻፍ ወይም ስለ አባበሉ ለማስረዳት አይደለም የተነሳሁት።
የዚህ መጣጥፍ ዓላማ ከምንስቅባቸው ነጥቦች አንዱ የሆነው የአስተርጓሚነት ወይም የመተርጎም ስልት
የዋናው ሃሳቤ አጫዋች ሆኖ ስላገኘሁት ነው። በጥሞና ይከታተሉኝ።

አንድ ወንድም ወደ አሜሪካ ለመምጣት ሲጠብቀው የነበረው ቀን ይደርስና የአሜሪካን ቆንስላ ተወካይ
ፊት በቃለ መጠይቅ አሜሪካ  ለመምጣት የሚያስችል አጥጋቢ ምክንያት እንዳለውና እንደሌለው ለመ
ፈተን ይጠራል። ወንድሜ ብሎ ከተመዘገበው ሰው ጋር በጣምራ ገብተው እየጠበቁ እንዳሉ ጠያቂዋ
መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ እንዲመቻት በተራ በተራ እንዲገቡ ታደርጋለች። እንግሊዘኛን ወደአማርኛ
እየቀየረ በሚናገር ሰው አስተርጓሚነት ሲመልስ ይቆይና ጠያቂዋ በድንገት እከሌ ወንድምህ  ለመሆኑ
ምን መረጃ አለህ? በመልክ በፍጹም አትመሳሰሉም ትለዋለች። ፍርጥም ብላ። አስተርጓሚውም የተቻለ
ውን ያህል አጥጋቢ መልስ እንደሚጠበቅበት ለማጉላት እየሞከረ አስተረጎመ። ተጠያቂው ይህንኑ በመረ
ደት ከመቀመጫው በመነሳት እጅ እየነሳ ልመናውን ማፍሰስ ጀመረ። አስተርጓሚው ያንን ሁሉ ልመና
ና ተማጽኖ አቀናብሮ ለማስተርጎም እንደሚከብደው ሲነግረው ጊዜ፤ መለስ አለና እሺ ባይሆን «የእናት
ሆድ ዝንጉርጉር ነው» ብለህ በአጭሩ አስረዳልኝ ብሎ ለመነው። አስተርጓሚውም  ግራ በመጋባት
ትንሽ አሰብ ካደረገ በኋላ «Mothers stomach like Zebra!» ብሎ እርፍ አለ።

የተረቱ እውነት መሆን እያንዳንዳችን በህይወታችን ውስጥ በሚያጋጥሙን ገጠመኞች ልናረጋግጥ ችለን
ይሆናል። እኔ ግን ዛሬ የእናት ሆድ ያልኩት ሀገራችንን ኢትዮጵያን ነው። በዝንጉርጉር የመሰልኩት
ደግሞ የሚሞቱላትንና የሚገድሏትን  ልጆቿን ልዩነት ነው። ተረቱ ውጫዊ መልክ ላይ ትኩረት ሲሰጥ
የኔ መጣጥፍ ደግሞ የውጭውን መልክ ከመጤፍ ባለመቁጠር የባህርይ ዝንጉርጉርነት ላይ ሂደቱን ያከና
ውናል።

መቼም እኔ ልነግራችሁ የተዘጋጀሁበት ነገር እንደ አዲስ ነገር የሚታይና ጉድ ጉድ የሚያሰኝ አይደለ
ም። ከጥንትም ጀምሮ በጥቂት ባንዳዎች ምክንያት የሃገር ድንበር ይደፈራል፤ የንጹሐን ዜጎች ደም
ይፈሳል፤ የታሪክ ቅርስ ይዘረፋል ይወድማል፤ በጠቅላላው የአንዲት  ሀገር  ብሔራዊ  ልዕልና  አደጋ
ውስጥ  ይወድቃል። ይሄ እንደ ዕጣ ፈንታ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ተደጋግሞ ተከስቶአል።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ኢትዮጵያ ሃገራችን በጣሊያን ሠራዊት ስትወረርና ብዙዎች የቁርጥ ቀን
ልጆቿ ዱር ቤቴ እያሉ ቤት ትዳራቸውን ኑሮ ሃብታቸውን እያፈረሱ ለውድ ህይወታቸው ሳይሳሱ የሃገ
ራቸውን ጥሪ በእለሁ ባይነት ሲመልሱ አጥንታቸውን ሲከሰክሱ ደማቸውን ከአፈሯ ጋር ሲለውሱ፤ ጥቂ
ቶች ባንዳዎች ደግሞ ለጠላት በማደር የወገን ሠራዊት በየት እንደተደበቀ፤ መሪው ማን እንደሆነ፤ የመ
ዋጋት ዐቅሙ ምን እንደሆነ፤ ቁሳዊና የአይዞህ ባይ ድጋፍ ከነማን እንደሚያገኝ ሳይጠየቁ ለጠላት መረ
ጃ በማቅረብ ለሹመትና ለሽልማት ሲራኮቱ እንደነበረ እነሱም እነማን እንደሆኑ ኢትዮጵያውያን አያቶ
ቻችንም ሆኑ አባቶቻችን በሹክሹክታ ስም እየጠሩ ሲያወሩ ሰምተናል።

አለመታደል ሆኖ ኢትዮጵያ ሃገራችን አንድ ሥር ከሰደዱ ችግሮቿ አንዱ የሆነው የትኛው ባንዳ የትኛ
ው የቁርጥ ቀን ልጇ እንደሆነ ለይቶ በግልጥ በአደባባይ መክሰስና መውቀስ፤ መሾምና መሸለም አታው
ቅም። ለዚህ ነው እሳይ እታች እያሉ ሲዋጉ፤ ሲዋደቁ የነበሩት  ጀግኖች  ልጆች ንጉሠ ነገስቱ ወደ
ዙፋናቸው ሲመለሱ በከተማ እያውደለደለ የነበረው ባንዳ በፍጥነት የባንዳነት ልብሱን፤ ስሙን፤ ምላሱ
ን ቀይሮ እፊታቸውሲቆም የሌሎችን የት መድረስ ሳያጣሩ፤  ገድላቸውን ሳይሰሙ ከተደበቁበት ከቀበሮ
ጉድጓድ  እየወጡ እንዲመጡ ሳይጠብቁ ሹመቱ ሽልማቱ ስለተካሄደ፤ብዙ ጀግኖችም ሁሉ ተደላድሎ
ካለቀ ስለደረሱ መቼም እሮሮን ለማሰማት ምቹ በሆነውና በኪን የተጌጠውን ቋንቋ ተጠቅመው፤

«ኢትዮጵያ ሃገሬ ሞኝ ነሽ ተላላ፤ የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ።»
ብለው ሆድ የሚያባባ ትምህርታዊ ነገር ጫር አድርገው ያለፉት። ታዲያ ሰሚ ቢኖር አልነበር?

ታዲያ ይህ ክፉ በሽታ በተረት ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ውስጥ ባንዳነትና፤ አድርባይነት፤ ለባለሥልጣን
አጎብድዶ መኖር መውደድ እንዲህ ባልተስፋፋ ነበር። ግን እናንተዬ ተረትና ተግባር ለየቅል ሆኑና
እኮ ተቸገርን!

እስቲ የአደባባይ ምስጢር ከሆነው ልጀምር። የጠቅላይ ምኒስቴር መለስ ዜናዊ አባት ነፍሳቸውን ይማረ
ውና በጣሊያን ጊዜ ባንዳ እንደነበሩ ሃገር አሳምሮ ያውቃል። እሳቸውም አያፍሩበትም። ታዲያ ይህን
እየሰማ ያደገው የአሁኑ ሃገረ ገዢ ሃገሪቷን በግላጭ ሲያገኛት በባንዳነትም በመሰለፍም ሆነ በሌላ ባገኘ
ው አጋጣሚ ጥፋቷን ቢያዘጋጅላት ለምን ይደንቀናል? ምክንያቱም ይኸ እንደ ጥፋት ተቆጥሮ ወላጅ
አባቱ ቅጣት ሲደርስባቸው በሕዝብ ዘንድና በታሪክ መዝገብ ላይ ከክብር ዝቅ ሲሉ አላየምና።
የመንደር ለመንደር ሐሜት እንማገን ጎድቷል?

በሌላ በኩል ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስን የመሰለ ታላቅ ጻድቅ አባት ለፋሺሽት መንግስት አልገዛም ከማለ
ት ሌላ፤ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ወታደር ውድ ሃገራቸው በሰጠቻቸው ሃይማኖታዊ መሣሪያ ጠላትን
ገስጸው፤ የሕዝቡ አንድነት ጥያቄ ውስጥ በወደቀበት ክፉ ጊዜ ብሔራዊ ስሜቱ እንዲቀሰቀስ ከራሱ በ
ፊት ሃገሩንና የሃገሩን ክብር እንዲያስቀድም ራሳቸውን የቡሄ ችቦ አድርገው በመለኮስ ለድሉ መቃረብ
ይኸ ነው የማይባል አስተዋጽዖ አበርክተው ሳለ፤ «ለዶግማዋ» አለመነካት የሞቱላት ቤተ ክርስቲያን
በጻድቅ ስም ስማቸውን ሳትዘክር መክረም አይገርምም? እኔን ይገርመኛል። ውድ ህይወታቸውን በደስታ
የሰዉላት ሃገርም ብሔራዊ ቀን ሳትሰጣቸው፤ በእውነት ለሳቸው ብቻ ሳይሆን እንደሳቸው ላሉ ሁሉ
መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ቀን አለመሰየሙ አይገርምም?
በዚሁ አንጻር ከሳቸው እኩል ሲመተ ጵጵስና ተቀብለው ግን ይህንን ታላቅ ኃላፊነት በመዘንጋት ከጠላ
ት ጋር በማበር አስኬማቸውን በወገን ደም ያቀለሙት አቡነ አብርሃም ስማቸው እንደተከበረ ይኖራል።
ከድተዋት የሄደችው ሃይማኖትም በምን ቀኖና መልሳ እንደተቀበለቻቸው ታሪክ የዘገበው ነገር መቼም
ያለ አይመስለኝም። ታዲያ ይሄ አይገርምም ትላላችሁ? እኔ ሁሌም ይገርመኛል።

ሰዎች በኃላፊነት ላይ ሲቀመጡ ኃላፊነታቸውን ሲወጡ ሊመሰገኑ ሳይወጡ ሲቀሩ ደግሞ እንደ አግባቡ
ሊወቀሱ ሊከሰሱ ግድ ነው። እዚህ ላይ በምኞት ዓለም ከሚኖሩት መካከል መቆጠር እንዳለብኝ የገባኝ
አሁን ነው። ለምን ብትሉኝ፤ በሃገራችን በኢትዮጵያ የተለመደው ወይም በሕዝቡ ዘንድ ጠቅላላ ተቀባ
ይነት አግኝቶ የሚኖረው አሠራር ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረው ዓይነት ነው።

በተለይ በአሁኑ ዘመን ከዚህ ዓለም ምቾትና ድሎት ጋር ምንም ኅብረትና አንድነት ሊኖረው የማይገባው
መንፈሳዊ ሹመት እንኳን ሳይቀር ከዚሁ ያልተለየ ባህርይ እየተላበሰ ይገኛል። በጠቅላላው የተሾመው
የመሰለውን ሲጠቅም ያልመሰለውን ለመጉዳት ሲያሳድድ፤ ሲያስር፤ ሲገርፍ፤ ሲገድል፤ መቆሚያ መቀ
መጫ አሳጥቶ ሲያሰድድ፤ የግል ጥቅም በማካበት ሲበለጽግ ነው የሚታየው። ያልተሾመውም አስኪሾ
ም ድረስ የምኞት ልጋግ እያላገ ዳር ቆሞ ቀን ሲጠብቅ ነው የሚታየው። ታዲያ የሃገራችን ልማድ
ተረትን በተረትነቱ ከማስተማር በቀር እንዴት ወደተግባር እንድንሸጋገር ምንም መፍትሄ አይሰነዝርም።
ምክንያቱም ቆማጣን ቆማጣ......ተብሎ ይተረታል እንጂ፤ አንተ ቆማጣ ነህና አትፈትፍት፤ ብሎ ግልጡን
የሚናገር የለም።

ለማንኛውም መልሼ ወደ እናት ሆድ ዝንጉርጉር ሃሳብ ልውሰዳችሁ። ታዲያ ይህ ዝንጉርጉነትን አጉል
ቶ የሚያሳይ ነገር በቅርቡ በአንድ ድህረ ገጽ ሳይ አስተዋልኩኝ። ይህ መልእክት ለአሁኑ የቫቲካን መሪ
ለሆኑት ፓትርያርክ የተጻፈ ነው። ይህ ደብዳቤ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ከሙሶሎኒ የጥፋት ሠራዊት
ጋር ያደረገችው ትብብር ስህተት መሆኑን አውቃ ይፋ የሆነ ይቅርታ ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ
እንድትጠይቅ የሚያሳስብ ነው። አንግዲህ ስታስቡት በአሁኑ ወቅት በሃገራችን ከዚያን ጊዜውም ባይወ
ዳደር ብዙ ግፍ እየተፈጸመ ነው። ቤተክርስቲያናችን ውስጥ ከመንግስት ወታደር ሸሽተው የተጠጉ ተ
ማሪዎች ተገፍተው ወጥተዋል፤ በሃገራችን ክርስቲያን በመሆናቸው ብቻ እስከ ህይወት መጥፋት ቤት ን
ብረት መወረስ፤ሲደርስባቸው ቤተክርስቲያን ምንም ዓይነት ግልጥ የተቃውሞ ድምጽ ሳታሰማ በዝምታ
አልፋለች ወዘተ...በመንግስት በኩል ያለውን መቼም በየጊዜው የጆሮአችንን ታንቡር ያደነቆረ በመሆኑ
እዚህ አልደግምላችሁም።

ይህ ድርጊት አጉልቶ የሚያሳየን ነጥብ ግን ዝንጉርጉር ከሆነው ማህጸን የወጡት የአንድ ሃገር ልጆች አንዱ ወገን ስላለፈው ጥፋት ሳይቀር እንቅልፍ አጥቶ ሲቆረቆር፤ አንዱ ወገን ደግሞ አዳዲስ ግፍ እየ ፈጠረ እንዴት ለራሱ እንደሚበለጽግ ያሰባልና እኒህ ሁለት ፍጹም የማይስማሙ እርስ በእርስ ተጠፋፊ ሃሳቦች የሚያራምዱ ሰዎች እንዴት የአንድ እናት ልጆች ሊባሉ ይችላሉ ነው? የሚከተለው ጥያቄ ደግ ሞ በየጊዜው በታሪክ ጥቁር ነጥብ ጥለው በሚያልፉ ባንዳዎች ረዳትነት የሚደርሰው ጉዳት የአሁኑ አልተስተካከለምና ላለፈው ግፍ የሚመለከተውን ሁሉ በተጠያቂነት ከመያዝስ እንቆጠብ?

ዓይናችን የሚያየው ጆሮአችን የሚሰማው ለስልጣን ሽሚያ ለግል ጥቅም ማጋበሻ ብቻ ስብዕናውን በመ ካድ ዓይኑን የታወረ ጅብ ይመስል ሌሊትና ቀን ለሆዳቸው የሚራወጡትን እያየን ምንም ለማድረግ አቅመ ቢስ ሆነናልና ያለፈውን ግፍ በዝምታ ማለፍ አለብን?

እኔ መቼም ሀሉም የድርሻውን ተወጥቶ ማንኛውም ግለሰብ በተሰለፈበት ዓላማ የሃገሩ የቁርጥ ቀን ልጅ ለመሆን ቢጥር ሁሉም በየፈርጁ ፍርዱን ሊቀበል ግድ ነው እላለሁ። ደግሞ እኮ አንድ ግዜ የእውነት ፍርድ ሚዛን ትልም ከተበጀለት ያለውም ሆነ የሚመጣው በዚያ እፈረጃለሁ ብሎ መፍራቱ አይቀሬ ነውና፤ የትናንት ግፍ የዛሬ አይደለም ብለን አንለፍ፤ ዛሬም በተራው ትናንት ሊሆን ግድ ነውና። ግን ግን የእናት ሆድ ዝንጉርጉር ከመሆን ምንም አይቀርም፤ ውጫዊ ዝንጉርጉርነትን ግን ለእናት ቤት መቆም ነው ወይስ የባህርይ ዝንጉርጉርነትም አስከትሎ የእናት ቤት ለማፍረስ ነው?

ሁሉም በየኅሊና ጓዳው ራሱን ይጠይቅ።

እኔ ለዛሬ በዚሁ ልሰናበታችሁ። ቸር ቆዩኝ!

ሰኔ–፳፱ ዓ.ም.